ሲሆኑ ከኅዳር 13 ቀን 1994 በኋላ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያወጡ ብቻ የመብቱ ተጠቃሚዎች ናቸው::/

መ/ የገቢ ግብር ነፃ ስለመሆን /በግብርና፣ አግሮ ፕሮሰሲንግ እና ማኑፋክቸሪንግ የሥራ መስክ ለተሰማሩ/፣

ናቸው::

*ከላይ በተጠቀሱት አዋጆችና ደንቦች መሠረት "የካፒታል ዕቃዎች" ማለት ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ የማምረቻና አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች፣ ዕቃዎችና አክሰሰሪዎች ማለት ነው:: መምሪያውም በዚሁ ትርጉም መሠረት ዕቃዎች እንዲገቡ ይፈቅዳል::*

## 4. ***ለገር ውስጥ እንዲገቡ የሚፈቀዱ ዕቃዎች***

### 4.1. ***ለአምራች/ግንባታ ድርጅቶች***

4.1.1. ማናቸውም ከምርት ሂደት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው መሣሪያዎች፣ እቃዎች አክሰሰሪዎችና የመለዋወጫ እቃዎች፣ ጀነሬተሮች፣ ለእቃ/ማቴሪያል አያያዝ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች/እቃዎች /Material Handling Equipments i.e. Fork lift, Trolley etc./ ጭምር ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ይፈቀዳል::

4.1.2. የግንባታ እቃዎች ለማስገባት የመንግሥት ፈቃድ ባገኘ ኮንሰልታንት የተዘጋጀ የጥሬ እቃ/ቁሳቁስ ፍጆታ መጠን /Bill of Quantity/ በማቅረብ ይፈቀዳል::

### 4.2. ***ለአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች***

4.2.1. በማበረታቻ የታቀፉ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው መሣሪያዎችና እቃዎች ከቀረጥ ነፃ ይገባሉ::

4.2.2. ለሆቴሎች /የኮከብ ደረጃ ያላቸው/

1. የቴሌፎን ማዞሪያ/PBX/፣ ኬብሎችና በመኝታ ክፍሉ ብዛት የስልክ ቀፎዎች፣
2. አልጋና ፍራሾች/ በክፍሉ ብዛት ልክ/፣
3. በእያንዳንዱ መኝታ ክፍል ውስጥ ቴሌቪዥንና፣ ፍሪጅ/በነጠላ/፣ ኮሚዲኖዎች፣ ቁም ሳጥኖች፣ የራስጌ መብራቶች፣ ሶፋዎች፣ /በጥንድ ወይም በነጠላ/፣

4. ለእንግዳ መቀበያ ክፍል የሚያገለግሉ ሶፋዎች፣ ጠረጴዛዎች፣ /ከተስተናጋጁ ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ በሆነ ብዛት/
5. የምግብ ቤት ወንበሮችና ጠረጴዛዎች /ከተስተናጋጁ ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ በሆነ ብዛት/፣
6. በመዋኛ ሥፍራ የሚቀመጡ የሽራ አልጋዎች፣ ጃንጥላዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ይፈቀዳል::

4.2.3. የቴሌ ኮንፈረንስን ለማካሄድ የሚውሉ ዕቃዎችና መሣሪያዎች የጉምሩክ ቀረጥ የሚከፈልባቸው ይሆናል::

4.3. ለመማር ማስተማር ሂደት የሚውሉ ኮምፒውተሮች ቀጥታ የትምህርት አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች በመሆናቸው ማንኛውም ተቋም የኮምፒውተር ጥያቄ ሲያቀርብ በአገባባቸውና አፈቃቀድ ላይ ጥንቃቄ እየተደረገና በትምህርት ተቋሙ የተጠየቀት ኮምፒውተሮች ብዛት ተቋሙ ሊያስተምር በእቅድ ከያዘው የትምህርት ዓይነትና ብዛት ጋር የተመጣጣነ ስለመሆኑ የማረጋገጫ ደብዳቤ ከትምህርት ሚኒስቴር በማቅረብ የቀረጥ ነፃ አገልግሎት ተጠቃሚነት መብት ይፈቀዳል::

4.4. <u>*ጥሬ ዕቃን በተመለከተ*</u>

4.4.1. ጥሬ እቃዎች የማምረቻ መሣሪያዎቹ ከገቡ በኋላ ለሙከራ ምርት /Commissioning/ በሚበቃ መጠን ለአንድ ጊዜ ብቻ በፍራንኮ ቫሉታ ቀረጥ ተከፍሎባቸው የሚገቡ ይሆናል::

4.4.2. የመገጣጠሚያ ፋብሪካዎች /Assembling Industries/ ጥሬ እቃዎቻቸውን በፍራንኮ ቫሉታ እና ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ አይፈቀድም::

4.5. *የቀረጥ ነፃ ዕቃዎች ዝውውርን በተመለከተ*

4.5.1. ማንኛውም ከቀረጥ ነፃ የገባ መሣሪያ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በተሰጠበት መስክ የሥራ ፈቃድ /Business License/ ሳይወጣ፣ በፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ወይም በክልል የፋይናንስ ቢሮዎች ለመንግሥት መከፈል ያለበትን የገቢ ግብር ስለመከፈሉ ማረጋገጫ ሳያቀርብ፣ መሣሪያው ቢያንስ ለ2 ዓመት አገልግሎት ሰጥቶና የጥገና ወጪው መጨመሩን የሚያሳይ ሰነድ ሳይቀርብ ወይም ተገቢው የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፈልበት በሽያጭ መልክ ለሌላ ወገን ማስተላለፍ አይቻልም::

- የኢንቨስትመንት ፈቃድ በተሰጠው ባለሀብት ወይም ድርጅት ሥም የተዘጋጀ የጭነት ሰነድ/አንድ ኮፒ/
- ባለሀብቱ/ ድርጅቱ በንግድ ሥም የሚጠቀም ከሆነ የንግድ ሥም ምዝገባ ምስክር ወረቀት/አንድ ኮፒ/
- ባለሀብቱ ግለሰብ ከሆነ ውጭ አገር ቋሚ ነዋሪ ስለመሆኑ ከሚኖርበት አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ የተጻፈና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ደብዳቤ /አንድ ኮፒ/
- ባለሀብቱ ማህበር ከሆነ ከኢምባሲ ደብዳቤ በተጨማሪ በውጭ ነዋሪው ባለአክሲዮን በአይነት የተደረገ መዋጮን የሚገልጽ ህጋዊ ሠነድ ማለትም/ የመመስረቻ ሰነድና የመተዳደሪያ ደንብ/ /አንድ ኮፒ/

5.4. <u>የፍራንኮ ቫሉታ መብት ተጠቃሚ የሆኑ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጋ ባለሀብቶች</u>

- የታደሰ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ኮፒ /ፕሮጀክቱ ሥራ የጀመረ ከሆነ የታደሰ የሥራ ፈቃድና/አንድ ኮፒ/
- የኢንቨስትመንት ፈቃድ በተሰጠው ባለሀብት ወይም ድርጅት ሥም የተዘጋጀ ኢንቮይስ፣
- የኢንቨስትመንት ፈቃድ በተሰጠው ባለሀብት ወይም ድርጅት ሥም የተዘጋጀ የጭነት ሰነድ/አንድ ኮፒ/
- ባለሀብቱ/ ድርጅቱ በንግድ ሥም የሚጠቀም ከሆነ የንግድ ሥም ምዝገባ ምስክር ወረቀት/አንድ ኮፒ/
- ባለሀብቱ ግለሰብ ከሆነ ከደህንነት ኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን የተሰጠ የመታወቂያ ደብተር /ቢጫ ካርድ/ /አንድ ኮፒ/
- ባለሀብቱ ማህበር ከሆነ ከመታወቂያ ደብተር በተጨማሪ በውጭ ዜጋው ባለአክሲዮን በአይነት የተደረገ መዋጮን የሚገልጽ ህጋዊ ሠነድ/መመስረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ/ /አንድ ኮፒ/

5.5. <u>ባለሀብቱ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ከቀረጥ ነፃ የገባ መሣሪያዎችን የገዛ ከሆነ</u>

- ቀደም ሲል ዕቃው ከቀረጥ ነፃ የገባ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ፣/አንድ ኮፒ/
- መሣሪያው በጊዜያዊነት ከቀረጥ ነፃ እንዲገባ የተዋዋለው የመንግስት አካል ፕሮጀክቱ በመጠናቀቁና ከአሁን በኋላ መሣሪያው የማያስፈልገው በመሆኑ በሽያጩ ላይ ተቃውሞ እንደሌለው የገለፀበት ሰነድ ፣
- የሽያጭ ውል፣/አንድ ኮፒ/

- ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ ሀገር ስለመግዛታቸው የሚገልጽ የማስጫኛ ሰነድ ወይም የካፒታል ዕቃዎቹ ከሀገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግዥ ውል ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር
- ፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት፣ የህንፃ ግንባታ፣ መሠረተ ልማት፣መጋዘን እና መንገድ የመሳሰሉት እየተሠሩ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት የክልል ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት የተጻፈ ማስረጃ፣

- ግንቦት 13 ቀን 1995 ዓ.ም ከወጣው የተሸከርካሪ መመሪያ በፊት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጡና በቀድሞው የተሸከርካሪ መመሪያ

የሚስተናገዱ ባለሃብቶች በፊት በነበረው አሠራር መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 5.9. ለአስጎብኚ ድርጅቶች /Tour Operators/ የሚያገለግል መኪና /አውቶቡስ/ ለማስገባት የሚያስፈልጉ ሰነዶች

- ማመልከቻ/በፅሁፍ/
- የኢንቨስትመንት ፈቃድ /የታደሠ/
- ኢንቮይስ
- የማስጫኛ ሰነድ
- የውጭ ምንዛሬ ያስፈቀዱበት ሰነድ ወይም ኢንዶርስ የተደረገ የማስጫኛ ሰነድ/ለሀገር ውስጥ ባለሀብት/
- የሚሠሩበት ቢሮ የግል ከሆነ የባለቤትነት ማስረጃ የኪራይ ከሆነ የኪራይ ውል/በውልና ማስረጃ የፀደቀ/
- ቢሮ ስለመከፈታቸውና በአስፈላጊ የመገናኛ ዘዴዎች/ስልክ፣ ፋክስ፣ ኢንተርኔት ወዘተ- - -/መደራጀታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ፣

## 5.10. በፍራንኮ ቫሉታ የሚመጡ ጥሬ እቃዎች

- ለማምረቻ መሣሪያዎች መሞከሪያና የሥራ ፈቃድ ለማውጣት የሚያስፈልግ የናሙና ምርቶችን ለማምረት የሚያገለግል ጥሬ ዕቃ በአንድ ጊዜ ጭነት ብቻ የጉምሩክ ቀረጥ ተከፍሎበት ይስተናገዳል፣
- በአሁኑ አዲስ አሠራር መሠረት የሥራ ፈቃድ ከመውጣቱ በፊት ከተለያዩ መ/ቤቶች ማለትም (ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ፣ጤና ጥበቃ፣ አካባቢ ጥበቃ፣ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር) አስተያየት አይጠይቅም፡፡ ስለዚህ መሣሪያዎቹን ማስገባቱ ሲረጋገጥ ለአንድ ጊዜ የጉምሩክ ቀረጥ ተከፍሎባቸው በፍራንኮ ቫሉታ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ይፈቀዳል፡፡

- 50% የሚሆነውን ምርታቸውን ለውጭ ገበያ የሳኩበት የባንክ ፊቃድና የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፣
- 75% የሚሆነውን የምርት ውጤታቸውን ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት በምርት ግብአትነት ስለማቅረባቸው የሚገልጽ የሽያጭ ደረሰኝ/Sales Invoice/ እና ገገር፡ የተረከበበትን ሰነድ/Receipt of the Exporter/ ማስረጃ፣

## 5.15. መንግስታዊ ያልሆኑ የእርዳታ ድርጅቶች ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፣

*5.15.1. መንግሥታዊ ያልሆኑ የእርዳታ ድርጅቶች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ለማግኘት የሚከተሉትን መረጃዎች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::*

- ፕሮጀክቱ በፌዴራል መንግሥት ወይም በክልል መስተዳድር መ/ቤት የፀደቀ ስለመሆኑ ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር የተደረሰ የስምምነት ሠነድ፣
- ስምምነት የተደረሰበት የፕሮጀክት ፕሮፖዛል
- ድርጅቱ በፍትሕ ሚኒስቴር ወይም በክልል የፍትሕ ቢሮ የተመዘገበ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የምሥክር ወረቀት:: ድርጅቱ እድሳት ስለማድረጉ የሚያረጋግጥ የታደሰ የማህበር ምዝገባ ሠርተፊኬት፣
- የማስጫኛ ሠነድ፣
- ኢንቮይስ፣/ፓኪንግ ሊስት/ በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ/
- የልማት ዕቃው በእርዳታ የተገኘ ከሆነ Donation Certificate፣
- የሚመለከተው የመንግሥት አካል የገፈው የትብብር ደብዳቤ
- ድርጅቱ ከፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ወይም በህግ ስልጣን ከተሰጠው የመንግስት አከል ጋር የተፈራረመው የGeneral Operational Agreement ሠነድ/ለመጀመሪያ የቀረጥ ነፃ ጥያቄ ብቻ/፣

### 5.15.2. የተሽከርካሪ የቀረጥ ነፃ የባለቤትነት ዝውውርን በተመለከተ

1. ተሽከርካሪው ወደ አገር ውስጥ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ መግባቱን የሚገልጽ ማስረጃ/ የጉምሩክ ዴክለራሲዬን፣ የቀረጥ ነፃ ፈቃድ ደብዳቤ/ ፣
2. የተሽከርካሪ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ/፣
3. ተሽከርካሪው በስጦታ የተገኘ ከሆነ የስጦታ የምስክር ወረቀት፣
4. ተሽከርካሪው በሽያጭ የሚዛወር ከሆነ የሽያጭ ውል ወይም የገንዘብ ደረሠኝ
5. ዝውውሩን በተመለከተ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተፃፈ የትብብር ደብዳቤ ፣
6. የፕሮጀክት ፕሮፖዛል እና የፕሮጀክት ስምምነት ሰነድ/ኮፒ/፣
7. የፍትህ ሠርተፍኬት /የታደሠ/፣

5.16. መንግስታዊ መ/ቤቶችና ድርጅቶች፣

- መሥሪያ ቤቱ/ድርጅቱ የፃፈው ማመልከቻ፣
- በጀት የተፈቀደለት ፕሮጀክት ፕሮፋይል፣
- የማስጫኛ ሰነድ፣
- ኢንቮይስ፣ ፖኪንግ ሊስት/በእንግሊዝኛ ወይም አማርኛ የተዘጋጀ/
- ከለጋሽ ድርጅቶች /ግለሰቦች በተደረገ ስምምነት መሠረት ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ለለጋሽ ድርጅቶቹ /ግለሰቦቹ የቀረበ የፕሮጀክት ዕቅድ/ፕሮፖዛል/፣ የስምምነት ሠነድና የስጦታ ምስክር ወረቀት /Donation Certificate/፣

5.17. የከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት የቀረጥ ነፃ መብት ለማግኘት የሚከተሉትን መረጃዎች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

- ተቋሙ የፃፈው ማመልከቻ፣
- የስምምነት ሠነድ እና የፕሮጀክት ጥናት፣
- የማስጫኛ ሠነድ፣
- ኢንቮይስ ፣ ፖኪንግ ሊስት/በእንግሊዝኛ ወይም አማርኛ የተዘጋጀ/፣
- የልማት ዕቃው በዕርዳታ የተገኘ ከሆነ Donation Certificate፣

